የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፭
አዲስ አበባ ኅዳር ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፪

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

6th Year No. 5
ADDIS ABABA - 2nd December, 1999

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፹፫/፲፱፻፺፪ ዓ.ም.
ከየመን ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገው ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ...................................................... ገጽ ፩ሺ፩፻፸፯

CONTENTS

Proclamation No. 183/1999
Ethio – Yemen Export Promotion Agencies Technical Cooperation Agreement Ratification Proclamation ........................................... Page 1177

## አዋጅ ቁጥር ፩፻፹፫/፲፱፻፺፪
## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ከየመን ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት ያደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በየመን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት እና ዋስትና ለመስጠት ሚያዝያ ፯ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም ሰንዓ ላይ ስምምነት የተፈረመ ስለሆነ፣

ስምምነቱን በሚገባ ሥራ ላይ የሚውለው በተዋዋይ ሀገር ሕጎች መሠረት ስምምነቱ መጽደቁን የሚያረጋግጡ ሰነዶች በዲፕሎማቲክ አካላት አማካኝነት ልውውጥ ከተደረገ ከ፴ ቀናት በኋላ እንደሚሆን በስምምነቱ ስለተገለጸ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኅዳር ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፪ ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት ከዚህ እንደሚከተለው ታውጇል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>
ይህ አዋጅ "ከየመን ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገው ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፹፫/፲፱፻፺፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· <u>ስምምነቱ ስለመጽደቁ</u>
በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በየመን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት በሰንዓ ሚያዝያ ፯ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ·ም የተፈረመው ስምምነት ጸድቋል።

## PROCLAMATION NO. 183/1999
## A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT ON RECIPROCAL PROMOTION AND PROTECTION OF INVESTMENT WITH THE REPUBLIC OF YEMEN

WHEREAS, an Agreement, on Reciprocal Promotion and Protection of Investment, between the Governments of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Yemen, was signed in Senea'a, Yemen, on the 15th day of April, 1999.

WHEREAS, it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall enter into force thirty days after the later date on which the Governments of the Contracting parties have notified each other in writing that their Constitutional requirements for the entry into force of the Agreement have been fulfilled;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the2nd day of Decmber, 1999;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-Article (1) and (12) of the Constitution, it is here by proclaimed as follows:

1. *Short Title*
This Proclamation may be cited as the "Reciprocal Promotion and Protection of Investment Agreement with the Republic of Yemen Ratification Proclamation No, 183/1999."

2. *Ratification of the Agreement*
The Agreement of Reciprocal Promotion and Protection of Investment signed in Sena'a Yemen on the 15th days of April 15, 1999 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Yemen is ratified.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፫· <u>የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ኃላፊነት</u>

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ስምምነቱን በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከህዳር ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ህዳር ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

3. Power of the Ethiopian Investment Authority

The Ethiopian Investment Authority is hereby empowered to implement the Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 2nd day of December, 1999.

Done at Addis Ababa, this 2nd day of December, 1999.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE